የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ወዝአደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር— መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ /መ.ኢ.ሶ.ን./ ልሣን

50

ቁጥር 41

ሰኔ 2፣1968

ርዕሰ አንቀጽ

የሰራተኛው የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ሠራተኞች ማህበራት ፌዴሬሽኖች 'ኅብረት'

የኢትዮጵያ ወዛደር በሙያ ማህበር ለመደራጀት ያደረገው ተጋድሎ የረዥም ጊዜና ብዙ መስዋዕትነት የጠየቀ ቢሆንም፣ በአመራር በኩል እስከዛሬም 'ያልታደለ' ሆኖ ቆይቷል። ወዛደሩ ከሥር በቁርጥነት ያካሄዳቸውን ትግሎች ከላይ የሚያደፈርሱበት፣ አቅጣጫ የሚያስቱበት 'ጠላቶች' በየጊዜው አጋጥመውታል። ወዛደሩ ከታች በወዛደራዊ ዓላማና መንፈስ የማይናቁ ድሎችን፣ ጥንካሬና ንቃት አግኝቷል። ከላይ በሚጠነጠንበት ሴራ ግን በተከታታይ 'ተሸንፏል'። በዚሁ ሴራ ምክንያትም፣ ሓሳቶቹ በወዛደሩ ትግል ተንተርሰው ከላይ ዝብ እያሉበት ኢሰማ ... እስከዛሬ ወዛደራዊ አመራር ሳያገኝ ቆይቷል።

የኢትዮጵያ ወዛደር፣ በመጀመሪያዎቹ የሙያ ማህበር ለማቋቋም ባደረጋቸው ትግሎች ድልን ተቀዳጅቶ ለምያማህበሩ መቋቋም በርግጥ የታገሉ የወዛደር መሪዎች የኢሰማን አመራር ያዙ። ፋሽስታዊው የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ይህን የወዛደሩ ትግል በርግጥ የርጥ አመራር በመግደል፣ በማሰርና በማሰቃየት አስወገደ። በቦታውም ከኢምፔሪያሊስቶችና ከመንግሥቱ ጋር በጥቅምና በዓሳማ የተሳሰረ አመራር ተካ። የኢትዮጵያ ወዛደር ከዚያን ጊዜ በኋላ ባንድ በኩል ከበዝባዦቹና ከኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጋር፣ በሌላ በኩል ከዚህ በጠላቶቹ ከተሿነባቸው አድሃሪ አመራር ጋር እየታገሉ እስከ የካቲት 1966ቱ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ድረስ መጡ።

በዚህ እንቅስቃሴም፣ የራሳቸውን የኑሮና የሥራ ሁኔታ ለማሻሻል ጥያቄዎቻቸውን፣ በአጠቃላይ በሰፊው ሕዝብ ጎኖች በኩል ለተነሱት ጥያቄዎች ተሰልፈው በመታገል ለተገኙት ድሎች ከፍተኛ ድርሻ አበርክተዋል። በነበየነ ሰለሞን የሚመራው የነኃይለ ሥላሴ 'ቅምጦች' ከኢሰማ አመራር ርጥተው ኢሰማ ለወዛደሩ የቆመ ድርጅት እንዲሆን ታገሉ። እንደገና፣ ቀደም ብሎ ከነበየነ ሰለሞን ጋር ተሰልፎ ኢሰማ 'ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት' የምትለውን አድሃሪ መፈክሩን እንዲያሰፍስት የጣረው የንዑስ ከበርቴ ደንፊና ቀለባሽ ቡድን፣ እነበየነ ሰለሞን ሲነሱለት፣ በዚሁ አጋጣሚ ተጠቅሞና አጋዦች ከአመራሩ ውስጥ ሰብስቦ ከወዛደሩ አናት ላይ ለመቆጣጠር ሞከረ።

ከዚያም ወዲህ፣ ወዛደሩን ባልተዘጋጀበት ትግል በማጋፈጥ አስመትቷል። የወዛደሩ ሙያ ማህበር ተጠናክሮ ወዛደሩን የሚያገለግል ድርጅት እንዳይሆንና የዚህ ቡድን ተቀጥያ ሆኖ እንዲኖር ታግሏል። ወዛደሩ ለራሱ ጥቅም ለመቆም እንዳይበቃና እርሱ በወዛደሩ ስም የያዘውን ማርናበዱ ለመቀጠል ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። ሀቀኛ ወዛደሮች ይህን የንዑስ ከበርቴ ደንፊና ቀለባሽ ቡድን፣ በኢሰማ አመራር ውስጥ ያሉትን ሰርጎ ገቦች ከመታገል ባይቆጠቡም፣ የዚህ ቡድን ምልምሎችና ሰርጎ ገቦች፣ በጠቅላላው የወዛደሩን እንቅስቃሴ አዳክመው እንደጎዱ፣ በተለይም ሙያ ማህበሩን መጠናከርና የወዛደሩ መገልገያ መሆን እንደገቱ ምንም ጥርጥር የለውም።

ኢሰማ ሲዘጋና በተለይም በኢሰማ አመራር አካባቢ የተሰገሰጉት ፀረ ወዛደር ድርጊቶች የአደባባይ ምስጢር እየሆኑ ሲሄዱ፣ ይህ የንዑስ ከበርቴ ደንፊና ቀለባሽ ቡድን በኢሰማ አመራር አካባቢ ለሚፈጽማቸው ፀረ ወዛደር ድርጊቶች ማጠናከሪያ 'ኢሳአማ'/የኢትዮጵያ ሳብአደሮች አብዮታዊ ማህበር/ የሚባል ድርጅት አቋቁሜያለሁ እያለ በመለፈፍ ላይ ይገኛል። ኢሳአማ የቆመለት ዓላማ ግልጽ ነው። የወዛደሩን መደብ ንቁ አባሎች ለመከፋፈል፣ የነዚህን ንቁ ወዛደሮችና የእውነተኛ አብዮታዊ ምሁራንን ሥምረት ለማደናቀፍ ነው። ወዛደሩ ፓሃል ርኅንበር ነዘት

ወዛደሩን የሚደዝሩ የሚጨብጡሩ ለማሳጣት ነው::በዚህም በደፈናው የወዛደሩን ትግል ብቻ ሳይሆን በተለይ የኢትዮጵያ አብዮት ዋስትና የሆነውን የአርሶነቱና ወዛደር ጋር ቱ መፈጠር ለማደናቀፍ ነው::ወዛደሩ ተመናክሮ፣ከአርሶአደሩና ከሌሎች ተራማጅ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር አንድነት ፈጥሮ ሌት ተቀን የሚጠነጥንበትን የፀረ አብዮት ሴራ ለመግታትና ለመምታት አስፈላጊውን ገና ትና ድርጅታዊ ጥንካሬ እንዳያገኝ ነው::

ይህ ለፀረ አብዮት ያደረ የንዑስ ከበርቴ ደጋፊና ቀለባሽ ቡድን የተነሳው የወዛደሩን ትግል ከሥሩ ሆኖ ለማዳከም ብቻ ሳይሆን ከላይ ሆኖም ትግሉን አቅጣጫ ለማሳጣት ጥምር ነው ለዚህም እስከዛሬ ያልቁ ተከታታይ ሙከራዎች አድርጓል::በቅርቡ የኢትዮጵያን ኢንዱስትሪ ሠራኖች አጠቃላይ ማህበር ለማቋቋም በተጠራው ጉባዔ አካባቢ የፈፀማቸው ሸፍጥ፣ኢዴሞክራሲያዊ እርምጃዎች የሚገነቡና ፀረ ወዛደር ድርጊቶች ለዚሁ ማረጋገጫ ናቸው::

ድርጅቱም ቢሆን፣የዚህ ቀለባሽ ቡድን ፍላጎት ከወዛደሩ ፍላጎት ተፃራሪ ነው::ለዚህም ነው በቀጥተኛና በአብዮታዊ መንገድ ከወዛደሩ ጋር መደባለቅን ሳይሆን፣ከወዛደሩ አናት ላይ በሴራና በጉንብድና ፈጢጥ ብሎ መፈንጠጥን የመረጠው::ደርጉ ያወጣው የሠራተኛው አዋጅ ፋሺስታዊ ነው፣ፋሺዝምን ለማጠናከር ነው፣አትደራጁ የሚለው ቅስቀሳው በወዛደሮች ቆራጥ ትግል ከሸፈበት::ቀለባሹ የአናርኪስት ቡድን የፈለገው ሳይሳካለት ቀረ::የኢትዮጵያ ወዛደሮች አዋጁ መሠረታዊ ጉዳዮችን በሚገባ ተረድተው፣ይህንና ሌላም ገና ብዙ የሚቀሩቸውን መሰናክሎች ለመወጣት ተደራጁ: ይህ ቡድን ግን ተስፋ አልቆረጠም::ተደራጅተው በስንት ትግል ሊያቋቁሙ ካቀዱት ማህበራቸው አናት ላይ ጉብ ለማለት ፀረ አብዮት ድርጊቶችን ማስፋፋት ጀመረ::በጉባዔው ለመካፈል ይቅርና ምንም ቦታ የማይሰሩ ምልምሎችን አሰርጎ አስገባ::ብዙ ሺ ወዛደሮችን የሚወክሉ መሪዎች በሽፍጥና በማናበድ እንዲወጡ አስደረገ::ጉባዔው ስለኢትዮጵያ ወዛደር አንገብጋቢ ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ጥያቄዎች መወያያ ሳይሆን፣የዚህ ቡድን ፀረ አብዮት መስመር ማፀደቂያ፣በመቅሳሰው የፀረ አብዮት ሴረኞች ማገዣ እንዲሆን ጣረ::

ከዚህ ፀረ አብዮት ቡድን ድርጊቶችም ሌላ፣በጉባዔው ዝግጅት በኩል በፍፁም የማይገቡ ጉዳዮች ነበሩ::በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ በሚከናወነው አሻጥር ምክንያት አንዳንድ የማህበር መሪዎች ሆን ብለው የማህበር መሪነት መታወቂያቸው በወቅቱ አልተሰጣቸውም:: ምንም ማህበር ለማይወክሉ አንዳንድ ግለሰቦች ግን የጉባዔ መግቢያ መታወቂያ ተሰጠ::ለአንዳንድ ማህበራት ስለጉባዔው መደረግ የተነገረው ጉባዔው አንድ ቀን ሲቀረው ነበር::የጉባዔው ተሳታፊዎች ሊሆኑ የማይችሉ የአናርኪስቱ ቡድን ምልምሎች ከጉባዔው አዳራሽ ሊገቡና ሊበጠብጡ የበቁት በነዚህ ኃይሎች ሁሉ ትብብር መሆኑ ግልጽ ነው::

ወኪሎቻቸው የተባረሩባቸው ወዛደሮች ከሌሎች ንቁ ወዛደሮች ጋር ተባብረው ይህ የሚገነብዱና ስብሰባ በሚካሄድበት ቦታና ጊዜ ተገኝተው ምሬታቸውን በታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ ገልፀዋል:: የተቀሩትም የኢትዮጵያ ወዛደሮች ወገን መስለው ሊበታትኗቸውና ትግላቸውን አቅጣጫ ሊያስቱባቸው የተነሱት ቀለባሽ አናርኪስቶች ከጀርባቸው ያውጠነጠኑባቸውን ሴራ ለማየት እድል አገኝተዋል:: ለጊዜው ቀለባሽ አናርኪስቶች ያቀዱት ሴራ አልተሳካላቸውም::የኢትዮጵያ ወዛደሮችም ለጊዜው አጠቃላይ ማህበራቸውን ለማቋቋም አልቻሉም::በዚህ ሁኔታም፣የኢትዮጵያ ወዛደሮች በሙሉ ከዚህ የቅርብ ጊዜ ድርጊቶች፣ካለፉት ከወዛደሩ ጀርባ እየተነሰሱ የወዛደሩን የሞያ ማህበር አመራር ወዛደራዊ መሆን ያላስቻሉ ሴራዎች ትምህርት ቀስመው፣ለወደፊቱ ለራሳቸው ጥቅም የሚውል የሞያ ማህበር ለማቋቋም በከፍተኛ ጥንቃቄና ንቃት መታገል አለባቸው::

ለዚህም፣በየፋብሪካው በሚቋቋሙ ማህበሮች፣የአፍ ደላዮችን ሳይሆን በርግጥ ለወዛደሩ ጥቅም የሚቆሙ የማህበር መሪዎችን በዲሞክራሲያዊ መንገድ መምረጥ አለባቸው::ንቁ ወዛደሮች ይህን ምርጫ ከዳር ቆመው ማየት የለባቸውም::ለዲሞክራሲያዊ አመራረጥና ለሀቀኛ የወዛደር ወገኖች መመረጥ በግንባር ቀደምነት መታገል አለባቸው::እነዚህ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የሚመረጡ የማህበር መሪዎች ለሚወስዱት እርምጃዎች ሁሉ ለመረጧቸው ወዛደሮች ተጠያቂ መሆን አለባቸው:: ከወዛደሩ ፍላጎትና ጥቅም ተፃራሪ የሆኑ እርምጃዎችን ሲወስዱ ሲገኙ በይፋ ተገዝው ቦታቸውን መልቀቅ አለባቸው::

በዚህ ሁኔታ የተመረጡ የሰዶ ለዶ ርዛደር፡ማህበራት መሪዎች አጠቃላይ ጉባዔ ከማድረጋ
ቸው በፊት የጉባዔው አጀንዳ ለየቅርንጫፍ ማህበራቱ በነዚህም በኩል ለርዛደሮች ሁሉ መቅረብ
አለበት::እያንዳንዱ የርዛደር ማህበር በአጀንዳው ላይ መነጋገር፣ሃሳቡን መግለጽ አለበት::የ/
ንዱ ቅ/ማህበር መሪ ርደአጠቃላዩ ጉባዔ ሲመጣ፣የመረጡት አባሎች በዲሞክራሲያዊ መንገድ ተደ
ይ ተውበት የደረሰበትን ሩሳኔ ይዞ መምጣትና በጉባዔው ላይ ቢካፈልም ይህንኑ ሩሳኔ ማንፀባረቅ
አለበት::በዚህ ጉባዔ ላይ የሚካፈል የርዛደር መሪ ተጠያቂነቱ ለመረጡት ርዛደሮች ነው::
ጉባዔውም፣እያንዳንዱ ቅ/ማህበር ተርያይቶበት ባፀደቀው አጀንዳና ርኪሎች ከየማህበራ
ቸው ባመጡት ሩሳኔ ላይ በመመርኰዝ መስራት አለበት::የዚህ ጉባዔም ሩሳኔ ቢቻል አጠቃላይ ስ
ባዔ ላይ የሚመረጠው የአጠቃላይ ማህበሩ አመራር እንደገና በዲሞክራሲያዊ መንገድ መመረጥ ይና
ርበታል::ከመርጠም የየትኛውም ቡድን ተቀጥያ ሳይሆን የጠቅላላ ጉባዔውን ሩሳኔ በሥራ ላይ የ
ሚያውልና የጠቅላላውን ርዛደር ጥቅምና መብት የሚያስከብር መሆን አለበት::ከላይ የዘረዘርነውን
ዲሞክራሲያዊ መንገገድ ካልተከተለ፣የርዛደሩ መደብ ሙያ ማህበር የዚህ መደብ መገልገለገያ ሊ
ሆን አይችልም::ከፀረ ርዛደር ቡድኖች መጠቀሚያነት ሊያልፍ አይችልም::የኢትዮጵያ ርዛደሮች
ባጠቃላይና ንቁ ርዛደሮች በተለይ ይህንን ሀቅ ተረድተው በርግጥ ሊያገለግላቸው የሚችል አጠቃ
ላይ ሙያ ድርጅት ለማቋቋም ብርቱ ትግል ማድረግ አለባቸው::
የኢትዮጵያ ተራማጆቸም የርዛደሩ መደብ ሙያ ድርጅት እንዲቋቋም በሚደረገው ትግል ገለ
ልተኛ ሊሆኑ አይችሉም::እንዲያ ከጭቁና ባለተላቀቀበት ሁኔታ፣ከሶሺያሊስት አብዮት በኋላም የር
ዛደሩ መደብ ሙያ ድርጅት ከፍተኛ ገለጋሉትና ቦታ አለው::ከቀሳ ጉደል ጅምላ መደቡን ሊይዝ
የሚችለው የርዛደሩ ሙያ ማህበር ብቻ ነው::ከኢኮኖሚያዊ ትግል ርደፖለቲካ ትግል፣ከስፖንታን
የስ ትግሉ ርደነቃና በራሱ ርአዕት ዓለም የታጠቀ ትግል ርዛደሩን የሚያሸጋገረው ድልድይ ይህ
ሙያ ማህበር ነው::የርዛደሩ ርአዕት ዓለም መቀስቀሻ ሜዳ፣የትግል መለማመጃ ት/ቤት ሙያ
ማህበሩ ነው::ታሪካዊ ግቡ ደርሶ ሥልጣን እስኪጨብጥ ድረስ የዘለቄታ ዓላማውን ሳይዘነጋ ለእ
ለታዊና ገዜያዊ ጥቅሞቹ መታገያ ድርጅቱ ይኸው ሙያ ማህበር ነው::
በኢትዮጵያ፣የርዛደሩ ሙያ ማህበር ከነዚህም አልፍ የተለየ ቦታ አለው::የርዛደሩ
ፓርቲ እስካሁንም ስላልተፈጠረ፣ሙያ ማህበሩ የዚህን ፓርቲ ቦታ ሊይዝ እንደማይችል ቢታርቅም፣
ይህ ፓርቲ እስኪፈጠር ድረስ ርዛደሩ በዚህ አብዮታዊ ትግል ሊያሳትፍ የሚችለው ሙያ ማህበሩ
ነው::በዛሬው የኢትዮጵያ ሁኔታም፣ፀረ አብዮት ሴራን ለመግታት ሆነ የተገኙትን ድሎች ለማስጠ
በቅ የርዛደሩ ተሳትፎ እጅግ አስፈላጊ ነው::ለዚህ ተሳትፎ ደግሞ እውነተኛ ርካዶን፣የርዛደር
ፓርቲውን እስኪያገኝ ድረስ ከዓር ሙ ለማየት አይቻልም::ዛሬ ባለው ድርጅት አማካይነት መታ
ገል አለበት::
ስለዚህም፣የኢትዮጵያ ሃቀኛ አብዮታውያን የርዛደሩን ትግል በሚመለከተው በኩል ሁለት
የሚደጋገፉ ቀዳሚና አጣዳፊ ተግባሮች አሉባቸው::ከንቁ ርዛደሮች ጋር ተባብረው የርዛደሩን
ፓርቲ ለመመስረት ከፍተኛ ትግል ማካሄድ አንደኛው ነው::ሁለተኛው፣ርዛደሩ የራሱ አገልጋይ የ
ሆነ አጠቃላይ ሙያ ማህበር ለማቋቋም በሚያደርገው ትግል ከጐኑ መሰለፍ፣ገቃትን እንዲያገኙ
እያገዙ ድሎችን ሊቁጥ የሚያሰፈስፉትን ቀለባሽ አናርኪስቶች ማጋለጥ ነው::
ለነዚህ ሁሉ ከገብ መድረስ ከርዛደሩ መደብ ጋር መዋሃድ ዓይነተኛውና መሰረታዊው መን
ገድ ነው::የርዛደሩን ንቁና ቁና ሳይገባዩ ሶሺያሊዝምን ለማዋሃድ እስካሁን ከተደረገው ከፍተኛ
ጥረት ይበልጥ ማድረግ አጣዳፊ ነው::የኢትዮጵያ ርዛደር በሰርጉ ገቦች እየተናበደ፣በፀረ አ
ብዮት ቀስቃባቸው ሕብረተ አየሳሳ ከሄደ የኢትዮጵያ አብዮት ምንም ፍስትና አይኖረውም::እውነ
ተኛ አብዮታውያንና ንቁ ርዛደሮች ከበረቱ ገን፣ትግላቸውን ካጣመሩ ገን፣የኢትዮጵያ ርዛደር ቀ
ለባሽ አናርኪስቶች የሚቀራመቱት ሳይሆን የኢትዮጵያን ሕዝቦች ትግል የሚመራ አብዮታዊ ኃይል
ይሆናል::

የርዛደሩን ንቁና ፩ ከፀረ ርዛደር ሰርጉ ገቦች እናጸዳ
የርዛደሩን ንቁና ፭ና ሶይገባዩ ርአዕተዓለሙን እና ዋሀዱ
ከርዛደሩ ጋር እንዋሃድ፣የርዛደሩን ፓርቲ እንገንባት

ሰገዶትና የኢኮኖሚ ችግር

በአገራችን በመፋፋም ላይ የሚገኘው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ከተቀጣጠለ ይኸው ሁለት ዓመት
ሙሉ ያህል ሆኖታል:: በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ትግል ያደረገው
ፈጣን እርምጃ በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: አብዮታዊው ትግል እንዲህ የተፋፋመው መሬቱን ይዞ
በሚገባ ሳይቀነባበርና በድርጅት ሳይመራ፤ በሕዝብ ተጥቆ ባይደገፍ ያስገኛቸው ድሎች ብዙ ናቸ
ው:: እነዚህን የሕዝብ ድሎች ባለፉት <u>የሰፊው ሕዝብ ድምጽ</u> እትሞቻችን ሳናነሳቸው ያለፍንበት
ጊዜ የለም::

ዛሬ በምንገኝበት ወቅት፤ የአብዮታችንን የወደፊት ግስጋሴ ሊገታ የሚችል አሳሳቢ ሁኔታ
በተጨባጭ መልኩ ከፊታችን ተደቅኖ እናያለን:: ይኸውም ሰፊው ሰርቶ አደር ሕዝብ የተዘፈቀበት
ታላቅ የኢኮኖሚ ችግር ነው:: ምንም እንኳ የአብዮት ጊዜ ቢሆን አገራችን የምትገኝበት የኢኮኖሚ
ሁኔታ እጅግ አስከፊ መሆኑ ለአብዮት ደጋፊዎች በሙሉ ግልጽ ሊሆን ይገባል:: የአስፈላጊ ዕቃዎች
ዋጋ ከመጠን በላይ እየጨመረ በመሄድ ላይ ነው:: አንዳንድ አስፈላጊ ሸቀጦችማ እስከነጭራሹ
ከገበያ ለማግኘት አስቸጋሪ ሆኗል:: የስኳር፤ የዘይት፤ የእንጨትና በተለይም የጤፍና የበርበሬ
ዋጋ ሬዘተ. በብዙ እጅ ወደሰማይ መጥቋል:: የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ደሞዝ ግን ካለበት አልተነቃ
ነቀም:: ይህ ጠቅላላ የኢኮኖሚ ችግር በጣም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ወዛደሩንና ሌሎች ሠርቶ
አደሮችን ይቅርና መካከለኛ ገቢ ያላቸውንም እንኳ ከተለቀ ችግር ጥሏቸዋል:: በሜይ አንድ የወ
ዛደሮች ቀን ተይዞ የነበረው " የጤፍ ዋጋ ሰለሳ፤ የወዛደሩ ደመወዝ ሰላሳ" የሚለው ሰሌዳ የ
ወዛደሩን እሮሮ የሚያንፀባርቅ ነው::

በእርግጥ በአንድ አገር ውስጥ አብዮት በሚደረግበት ወቅት የኢኮኖሚ ችግር አለ:: ወደ
ኋላ መለስ ብለን ብንመለከት ለየካቲት 1966 አብዮታዊ ሁኔታ መፈጠር ምክንያት ከሆኑት አን
ዱ ይኸው የኢኮኖሚ ችግር ነው:: የየካቲት እንቅስቃሴ እንደዚያ ሕብረተሰባዊ መደቦችንና ክፍ
ሎችን አስተባብሮ እንዲነሱ ካደረገበት ምክንያቶች የኑሮ ዋጋ መናርና በአጠቃላይ የኢኮኖሚ
ችግር መባባስ እንደነበረ የሚታወስ ነው::

ባለንበት በዛሬው ወቅት አገሪቷን የገጠማት የኢኮኖሚ ችግር ለየካቲት እንቅስቃሴ መነሻ
ከሆኑት ችግሮች የተረሰ ቢሆንም፤ የዛሬው የኢኮኖሚ ችግር ግን ከየካቲት 1966ቱ ጋር በእ
ኩል ዓይን የሚታይ አይደለም:: የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶች በመንግስት እጅ በመግባታቸው
የጥቅም ምንጫቸው የቀረባቸው አቀባባይና ቢሮክራት ከበርቴዎች ምርት እንዲቀረቅዝ ያደርጋሉ::
ሸቀጣ ሸቀጦች በተስተካከለ ዘዴ ለገበያ እንዳይቀርብ ታላቅ ቀውስ ይፈጥራሉ:: የከተማ ትርፍ
ቤትና ቦታ የተረሰባቸው፤ ሌሎችም ገና ለገና ይረሰብናል ብለው የሚሰጉ እንደ የትራንስፖር
ት ንብረት ባለቤቶች ያላቸውን ተቀማጭ ገንዘብ ከባንክና ከመሰሰሉት በከፍተኛ እጅ እያወጡ
ያባክናሉ:: ይህ ራሱ በሸቀጣ ሸቀጡ ላይ ከፍተኛ ጥያቄ/የመግዛት ፍላጎት/ስለሚያስከትል ለዋ
ጋ መናርና ለሸቀጥ እጥረት ምክንያት ሆኗል:: ከዚሁ ጋር ጠቀስ ለማድረግ የሚቻለው፤ የገጠሩ
መሬት ለአራሹ ገበሬ ከተመለሰ ወዲህ ገበሬው ምርቱን ሸጦ በሚያገኘው ገንዘብ ለኑሮው አስፈ
ላጊ የሆኑ ሸቀጦችን ከድሮው በበለጠ መጠን ለመግዛት ስለሚሻ ለእቃ እጥረት ተጨማሪ ምክንያት
እንደሆነ ነው:: ከዚሁ ጋር የአሃራዊ ሀብት ልማትና የንግድ ሚኒስቴር የመሰሰሉት የቢሮክራ
ሲው አካላት ችግሩ እንዲባባሱ የሚሸርቡት ራሱን የቻለ አሻጥር አለ::

በአብዮት ወቅት የሚገጥመውን የኢኮኖሚ ቀውስ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ለማስተካከል የረጋ
ሁኔታን፤ የአብዮታዊውን ትግል ከግብ መድረስ ይጠይቃል:: አብዮት ከግቡ ባይደርስ አብዮታዊው
ትግል ፋታ ሰጥቶ የኢኮኖሚውን ችግር በማስቀደም ችግሩን ለመድፈን ባለ ኃይል ሁሉ መሰለፍ
አይቻለም:: እንኳን አብዮት ግቡን ባልመታበትና ሰፊው ሕዝብ ስልጣን ባልጨበጠበት የአገራችን
ሁኔታ ይቅርና፤ በሩሲያ ውስጥ በነሌኒን መርቶ ወዛደሩ ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ የሰፊው ሕዝብ
የኑሮ ችግር ተባብሶ ነበር::

ይህ ስለተባለ ግን፤ አብዮታዊ ሁኔታ ባለ የኢኮኖሚ ችግር ይኖራል፤ ስለዚህ አዲስ ነገር
አይደለም፤ አስቸኳይ መፍትሄ መሻት አያስፈልገም ማለት አይደለም:: የዚህ ኢኮኖሚያዊ ችግር መንር

በአብዮታዊው ትግል ላይ የሚያስከትለው ጉዳት በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ ይህንኑ በመገንዘብ የኢኮኖሚውን ችግር ለማባባስ አድሃሪ ኃይሎች የማይገለብጡት ድንጋይ አይገኝም፡፡ ስለዚህም፣ በዚሁ አብዮታዊ ትግል ውስጥ እያለንም የኢኮኖሚው ችግር ሙሉ በሙሉ ባይርገድ እንኳ ጋብ የሚልበትን መንገድ፣ የአድሃሪዎች አሻጥር የሚከሸፍበትን ብልሃት መመርመርና ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

የኑሮ ውድነት፣ የሥራ አጥ መብዛት፣ ወዘተ. በአጠቃላይ የሰፊው ሕዝብ ምሬት መብዛት ለፀረ አብዮት ቀለበሳ የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ፀረ ሕዝብ ኃይሎች አብዮትን የሚቃወሙት በደፈናው የአብዮትን ግብ አንቀበልም በማለት አይደለም፡፡ እነዚህን የሰፊው ሕዝብ ምሬቶች በመጠቀም አብዮትን ያጥላላሉ፡፡ በኢትዮጵያ ሁኔታም፣ "ለውጥ ለውጥ ብላችሁ ታገላችሁ ከኃይለ ሥላሴ ጊዜ የባሰ የመጣባችሁ ነው" በሚለው ቅስቀሳ ላይ ይሰማራሉ፡፡ ሶሺያሊዝም በቃል ብቻ የተቀባ ስርዓት ነው ብሉ መለፈፍ ይቀናቸዋል፡፡ ሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ ትግሉ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ እለታዊ ችግሮቹን ሲያስወግድለት ስለማያይም፣ እነዚህ አድሃሪዎች በዚሁ ተጠቅመው በአብዮታዊ ትግሉ ላይ እምነት እንዲያጣ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ እንደዚህ ዓይነቱም ሰበካ፣ ለፀረ አብዮት ቀለበሳቸው ፖለቲካዊ ዝግጅት መሆኑ ነው፡፡ የቀናቸው ለት "ከውድቀት ልናድንህ መጣን" ለማለት ያመቻቻሉና፡፡

አብዮትን በተስተካከለና አቅጣጫ ወደፊት ማራመድ የማይሳካላቸው፣ በርግጥም ለሰፊው ሕዝብ እለታዊ ችግሮች መፍትሄ ለማምጣት የሚያስችል መንገድ ለመጠቀም የሚያቅታቸው አናርኪስቶችና አብዮትን የከዱ ቀለባሾች የሚጠቀሙት በዚሁ በሰፊው ሕዝብ ችግር፣ በቀሰሉ እንጨት በመስደድ ነው፡፡ በቅርቡ በቢሾፍቱ፣ በአዳማና በሻሸመኔ ቀለባሽ አናርኪስት ቡድንና ሌሎችም አድሃሪዎች ሥራ አጡን በብዛት አነሳስተው በማሰለፍ "በሶሺያሊዝም ሥርዐት ውስጥ የግል ሃብት አይኖርም" በሚል የተፈናበደ መፈክር ሰበብ ጥቃቅን ሀብቶችን፣ ጋሪና የፀጉር ማስተካከያዎች ሳይቀሩ፣ የ"መውረስ" እርምጃዎች አስወስደው ነበር፡፡ ይህን ዓይነቶቹ እርምጃዎች፣ በስቃይ ላይ የሚገኙትን ሥራ አጥና ሌሎችንም ከማደናበድ በስተቀር ለችግሮቹ ምንም መፍትሄ የማያመጡ ናቸው፡፡ አብዮትን በዛሬው ደረጃ የማይፈልጉ ኃይሎችን ወደ ፀረ አብዮት ድንኳን በመወርወር የጠላትን ሰፈር ማጠናከርም ነው፡፡ በጠቅላላው ሁኔታውን አተራምሶ፣ ለአብዮቱ የሚታገሉ ኃይሎችን አቅጣጫ አስቶና ነጣጥሎ፣ ከጀርባችን ፀረ አብዮት አመጽ ለሚያዘጋጁ ጠላቶቻችን ዕድልና ፋታ መስጠትና በገርገሩ ከላያችን ገብ እንዲሉ ለመርዳት ነው፡፡

እንደገናም፣ በገጠር የሚሰቃየው ሠርቶ አደር፣ የነዚህን ችግሮች ምንነት፣ የሚፈቱበትን ዘዴ ጠንቅቆ ለመረዳት ከፍተኛ የፖለቲካ ንቃት ያስፈልገዋል፡፡ በዛሬ ችግሩ ምክንያት ተጥቃን እንዳይፈታ፣ አብዮታዊው ትግሉ ቀጥሎ በዚሁ አማካይነት ለችግሮቹ መፍትሄ እያበጀና እየታገለ እንዲሄድ እንደዚሁ ከፍተኛ የፖለቲካ ንቃት ያስፈልገዋል፡፡ የኢኮኖሚው ችግር ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ መሄድ ደግሞ ለወዛደሩና ለሠርቶ አደሩ የፖለቲካ ንቃት እድገት እንቅፋት ነው፡፡ ባገራችን ሳይንሳዊ ርእዮተ ዓለም ላይ የተመረኮዘ ቅስቀሳ በሰፊው ሕዝብ መሃል መካሄድ ከጀመረ ጊዜው በጣም ቅርብ ነው፡፡ በመሰረቱ ይኸ ርእዮተ ዓለም ዛሬም በሰፊው ሕዝብ መሃል ገና ሥር አልሰደደም፡፡ በዕለት ኑሮው የሚሰቃየውን ሠርቶ አደር ደግሞ ጊዜያዊ ችግሩ ጋብ የሚልበትን ዘዴና ብልሃት ሳይፈጥሩለት ርእዮተ ዓለሙን እንዲቀስም ብቻ ለማድረግ ሰላሳ ጊዜ ቢሞከር ውጤቱ የሚፈለገውን ያህል ሊሆን አይችልም፡፡ በቅርቡ በተጀመረው የውይይት ክበቦች፣ በብዙ ቦታ ከርእዮተ ዓለም ትምህርት ይልቅ በዕለታዊ ችግሮች ላይ ለመወያየት መሞከሩ አንዱ መሰረታዊ መደገፊያ እንደሌለው ለመቁጠር አይቻልም፡፡ ይኸውም ባለንበት ሰዓት የሠርቶ አደሩ ዕለታዊ ችግር ፋታ የማይሰጥ መሁኑን ነው፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ የቀለባሽ አናርኪስቶችና የአድሃሪዎች የውንብድና የማጥላላት ዘመቻ አለ፡፡ ከሰለጠኑ አድሃሪዎች እንኳ አንዳንዶቹ ሳይንሳዊ ርእዮተ ዓለምን ፊት ለፊት በማጥላላት አይሰለፉም፡፡ ይህ ሳይንስ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ይቅርና በአገራችንም ኃያልነቱን እያስመሰከረ መጥቷልና፡፡ በዚሁም ምክንያት አድሃሪዎቹም ሆኑ ቀለባሽ አናርኪስቶቹ "የለት ዳቦህን ሳታገኝ ዳቦ በረዲዮ/በሬዲዮ የሚተላለፉትን አብዮታዊ ትምህርቶች ለማለት ነው፡፡/በልተህ ልትኖር ነው?" ማለት ጀምረዋል፡፡ ወዛደሩና ሠርቶ አደሩ ከእለታዊ ችግሮቹ አልፎ ለዘላቂ

ጥቅሙ ሊያስለፈው የሚያስችለውን ጉቶት እንዳያገኙ ይጣደፋሉ። ይህን ጉቶት ካገኙ በነርሱ ፀረ አብዮት ቅስቀሳ ሊፈታ እንደማይችል ጠንቅቀው ያውቃሉ።

እንግዲህ፣ እነዚህ ሁሉ አንድ ላይ ሲያያዙ፣ የኢኮኖሚ ችግር መኖር ለአብዮቱ በተከከለና አቅጣጫ ወደፊት መቀጠል እንቅፋት እንደሚሆን እናያለን። አድሃሪ ኃይሎች ያለውን ችግር ለማባባስ በየፈርጁ ጕርጓዶ ሲቆፍሩ እንመለከታለን። የኢኮኖሚ ችግር አብዮቱን ለመቀጠል የሚኖረው እንቅፋትነት ብቻም ሳይሆን አድሃሪ ኃይሎች ይህን የሰፊው ሕዝብ ምሬት እያባባሱ በመጠቀም የሚያካሂዱት ቅስቀሳ ላፀረ አብዮት ሁኔታውን የሚያመቻች ነው። ሂትለር ሥልጣን ላይ ለመውጣት ካደረጋቸው ዋነኛ ተግሎች አንዱ፣ በሕዝብ ሥቃይ ላይ እየተመረኰዘ ያደረገው 'ለብ ነኪ' ቅስቀሳ ነው። ከአሌንዴ መውደቅ ቀደም ብዩ ለፋሺስቶች ሥልጣን ላይ መውጣት መንገዱ የጠረገው ቅስቀሳ በዚሁ የሰፊው ሕዝብ ዕለታዊ ችግሮች ሳባቢ የተደረገ ነው። ስለዚህም የዛሬው የአገራችን የኢኮኖሚ ችግር በቀላሉ የሚታለፍ ሳይሆን፣ የአብዮቱን እድል ከሚወስኑት ከፍተኛ ጉዳዮች እንደ አንዱ መታየት አለበት።

በበኩላችን አስቸኳይ መፍትሄዎች ናቸው ወደምንላቸው ሳንሄድ ገን፣ ይህ የኢኮኖሚ ችግር እንዲባባስ የሚያደርጉትን ኃይሎችና ዘዴያቸውን መመርመር አለብን።

ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ዕቃዎች ከአምራቹ ወደ ሸማቹ የሚያስተላልፉት ነጋዴዎች ናቸው። የአገራችን ነጋዴዎች፣ በተለይ ከፍተኛዎቹ፣ በየካቲት እንቅስቃሴ ጥቅማቸው ተነክቷል። አብዮቱን ከሚፃረሩ ኃይሎች ጋር ተሰልፈዋል። ጥቅማቸው እስከዚህም ያልተነካ አንዳንዱ ነጋዴዎችም አብዮቱ ከቀጠለ እናንም ያስጋናል በሚል ፍርሃት በርግገው ከፀረ አብዮት ተደባልቀዋል። ስለዚህ አብዮቱን ለመቀልበስ የሚያመቹ አሻጥሮችን ከመሥራት ወደኋላ አይሉም። በዝቅተኛ ዋጋ ከአምራቹ የገዙትን በከፍተኛ ዋጋ ለሸማቹ ይሸጣሉ። በሌላ በኩል፣ 'ከኃይለ ሥላሴ ዘመን የባሰ መጣ' እንዲባልላቸው ከአምራቹ የገዙትን ዕቃ በመጋዘናቸው ይዘጉበታል፣ ከገበያ እንዲጠፋ ያደርጋሉ። /የአንዳንዱ አስፈላጊ ሸቀጦችን ዋጋ አጠመር መጥቀስ ቢያስፈልግ፣ ለምሳሌ በያዝነው ፣1968፣ ከየካቲት እስከ መጋቢት ባለው የአንድ ወር ጊዜ ብቻ፣ የምግብ ዋጋ 6.9 በመቶ ከፍ ብሏል። እህል 2.0 በመቶ፣ ሥጋ 23.5 በመቶ፣ አሳ 3.6 በመቶ፣ ከቀንድ ከብቶች የሚገኙ እንደ ወተትና ቅቤ የመሳሰሉት 11 በመቶ፣ ቅመማ ቅመም 14.9 በመቶ ዋጋቸው ከፍ ብሏል።

በዚህም ላይ ፣ ማከፋፈያ ድርጅቶች /በተለይም ከውጭ ለሚመጡ ዕቃዎች/ አሁንም አብዮቱን በሚፃረሩ ኃይሎች እጅ ናቸው። የነዚህም አሻጥር ሁለት ፈርጅ አለው። ባንድ በኩል በተጭበረበረ ፋክቱር የሃገሪቷን ሃብት ወደውጭ ያሸሻሉ። የውጭ አገር ደንበኞቻቸው፣ ኢትዮጵያ በምትገኝበት አብዮታዊ እንቅስቃሴ፣ እንኳን ፋክቱር በማጭበርበር ይቅርና በሌላም ብዙ ብዙ ነገሮች እንደሚረዷቸው ገልጽ ነው። በሌላ በኩል፣ የገባው ዕቃ በተከከለ እንዳይከፋፈል አሻጥር ይሰራሉ። ዕቃው የሚፈለግበት ቦታ እንዳይደርስ፣ ዋጋው ከሚገባው በላይ እንዲወደድ ያደርጋሉ።

የኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶች መሃል ከፍተኛ የሥራ ክፍፍልና ሕብረት አለ። ይህም አብዮቱ ራሱ ሲያድር የሚጨምር ነገር ነው። ፊውዳሎች በጫካና በውጭም እየተደራጁ በግልጽ አብዮቱን ይፃረራሉ። ነጋዴው በመስኩ በልዩ ልዩ አሻጥሮች ለፀረ ሕዝብ ኃይሎች አመጽ ሁኔታውን የሚያመቻች ሚና ወስዷል። ከኃይለ ሥላሴ የተረሰው ቢሮክራሲ በበኩሉ በሥልጣኑ እየተጠቀመ፣ እራሱም አሻጥር እየሰራ፣ የሌሎችንም አሻጥር እንዳላየ እያየና ቦታም እየሰጠ የራሱን ፀረ አብዮት ድርሻ ያበረክታል።

እንደ ብሄራዊ ሀብት ልማት የመሳሰሉት በአገሪቱ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ላይ የሚፈጽሙት ወንጀል ዛሬ ለብዙሃኑ ተራማጆች ስውር አይደለም። በቁጥጥራቸው ሥር እንዲውሉ በተደረጉት የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶች የተጠበቀባቸውን የምርት ውጤት ለማስገኘት ሳይችሉ ቀርተው አብዛኞቹ በኪሳራ ላይ ይገኛሉ። ብሄራዊ ሀብት ልማት ከመንግስት እርሻዎች በጊዜው ምርት እንዲሰበሰብ ሳያደርግ በመቅረቱ እህሉ እዚያው ታጭዶ በተመረበት ቦታ እስከመበስበስ የደረሰበት አንድ ሁለት የሚባል አይደለም። በርሊባ አካባቢ ብቻ እስከ ሃያ ሺህ ኩንታል በቆሎ ከአገልግሎት ውጭ ሆኖአል። በአሩሲና በሸለቆው አካባቢም የእህል መበስበስ ደርሷል። በአናጠ ሸለቆ እንዲ

ሁ·በብዙ መቶ ኩንታል የሚቆጠር ጥጥ የተከመረበት ቦታ እስከመኖለም ደርሷል::በብሄራዊ ሀብት
ልማት እጅ በሚገኙት የከብት እርባታ ጣቢያዎች የሚገኙት የቀንድ ከብቶች አስፈላጊው እንክብ
ካቤ ሳይደረግላቸው ፋርቶ የሞቱት ቁጥራቸው በቀላሉ የሚገመት አይደለም::በፋብሪካና በኢንዱ
ስትሪ አካባቢም የምርት ውጤት እንዲያቆረቁዝ፣በነዚህ ውስጥና በእርሻ ሥራ በተሰማሩት ወዛ
ደሮችና ሠርቶ አደሮች. የሚፈጠረው ገፍ ሁኔታውን ለመቀለበስ ሀገ ተበሉ የሚደረገ አሻጥር መሀ
ቱን ማገም ሊረዳው ይቻላል::ሠርቶ አደሩ በተደጋገመ ጊዜ በብሄራዊ ሀብት ልማት ላይ አርር
ውግና አቤቱታውን ማሰማቱ የታወቀ ቢሆንም፣በአድሃሪያ ባለሥልጣኖችና የኩርፖሬሽኑ ሃላፊዎች
ላይ በመንገስቱ በኩል እስካሁን የተወሰደ እርምጃ የለም::

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርም እንዲሁ ብዙ የኢኮኖሚ አሻጥር የሚፈፀምበት፣የተበሻ
ቀጠና ዝቅሳሳ ኩረንበን የነገሰበት የቢሮክራሲው አንዱ ክፍል ነው::ዛሬ፣እንኳንስ ለወዛደሩና
ለአርሶአደሩ ይቀርና በመ ዘሰና ገቢ አገኘው ከተማ እንኳን የሚጣጣ ሸቀጥ ናጋ እንዲህ በመና
ር ላይ እያለ፣የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የናጋ ቁጥጥር ለማድረግ ዳር ዳር ሲል እንኳ
አይታይም::ባለው የኢኮኖሚ ችግር የተነሳ፣ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ለምግብ የሚያገለገሉና
ሌሎችም ሸቀጦች ለነጋዴም ሆነ ለሸማቾች በከፍፍል/ራሺን/መልክ እንዲዳረስ የማድረጉ ሙከራ
የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን ፍራሸ የሚያሳስበው አይደለም::ከዚህም አልፎ፣ከትሳልቅ ነጋ
ዴዎች ጋር/ከሮጥያቹ ጥምር/ በጥቅምና በጉቦ እንደሸረሪት ድር የተሳሰሩ አድሃሪና የተገሚ
ቢሮክራቶች ስላሉ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በዕለት ችግሩ ቲጥር እንዲያዝና ለቀለባሾች መሳሪያ
እንዲሆን ተለቀ አሻጥር ይፈትላሉ::

በለብሄራዊ ሀብት ልማት አንዱ ሌላ ጉዳይ መጥቀስ ቢያስፈልግ፣በአሁኑ ጊዜ በከተማው
የወተት እጥረት ቢኖር ይህም ዱር ከሚገኘው በአንዱ አራተኛ ዝቅ ብሏል::የሚገርመው ግን፣
ከዓለም ባንክ በተገኘው ብድር ለወተት ኢንዱስትሪ ማስፋፊያ ተብሉ ወደ 2 ሚሊዮን ብር የሚ
ያርጣ ገንዘብ የተገዛ መሳሪያ አገልገሉት ላይ እንዳይውል ብሄራዊ ሀብት ልማት ካሸገው ሁለት
ዓመት ሆኖታል::የብሄራዊ ሀብት ልማት የዕቃ ግዥ ክፍል ከእነ ሚቹል ኩትስና ከመሳሰሉት የ
ውጭ አገር ካፒታሊስቶች ድርጅቶች ጋር በመመሳጠር ሌሎች አሻጥሮችን እንደሚሰራም የታወቀ ነው::

ከነጋዴዎች፣ከአድሃሪ ቢሮክራቶች ሌላም፣የንዑስ ከበርቴው ቀለባሽ አናርኪስት ቡድን
በዚሁ የኢኮኖሚ ችግር እንዳቀሚቷ የፀረ አብዮት ድርሻ ተሰጥቶታል::ለምሳሌ በርሲቦ አካባቢ
አርሶ አደሮች እህላቸውን ከተማ እንዳይሸጡ ሰፊ ቅስቀሳ አካሄደ::መልሶ ለከተሜው ገበሬው
እህል አለሸጥ አለ ምን ይናጣቸው?ወዘተ. የሚል ቅስቀሳ ያዘ::ይህ ድርጊት ባንዱ በኩል በአ
ርሶአደሩና በከተማው ሠርቶ አደር መሃል መቃቃር እንዲፈጠር ለማድረግ ነው::በሌላ በኩል የ
ከተማውን ሠርቶ አደር ችግር በማባባስ፣በፀረ አብዮት ቅስቀሳ እንዲፈታ ለማመቻቸት ነው::

በሌላ በኩል፣/በሐረር ክፍለ ሃገር/እንደዚሁ አርሶ አደሩን በበሬ እተረሰ፣መንግስት
የሮረባቸው ትራክተሮች ሊያርሱልህ ይገባል በሚል ቅስቀሳ አርሶአደሩን አሳምነው በሬውን አሸ
ጡ::የእርሻው ወቅት ሲደርስ የአካባቢው ትራክተር ነጂዎች ሥራ እንዲያቆሙ ቀስቀሰ ያዙ::
ትርክተር ያርስልናል ብሉ በሬዎችን የሸጠው አርሶአደር በምኑ ይረስ? ካላረሰ ምን ይበላ?
ካልበላ እንዴት አብዮቱን ከግቡ ያድርስ?ቀለባሽ አናርኪስቶች የፈለጉትም የዚህ ዓይነቱን
ሁኔታ መፈጠር ነው::ይህም ብቻ ሳይሆን አርሶአደሩ የሚገዛው ከነርሱ ጋር ሳይሆን ከትራክተር
ነጂዎች ጋር በመሆኑ፣እንደገና ለኢትዮጵያ አብዮት ፍስትና ለሆነው ወዛደር አርሶአደር ሕብረት
መሰናክል መሰራታቸው ነው::

እንግዲህ፣የአገራችን የኢኮኖሚ ችግር መፍትሄ እንዲያገኝ ብቻ ሳይሆን እንዲባባስ
የሚጥሩት የኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶች በምላሳ ናቸው::ይህም የዚሁ ኢኮኖሚያዊ ችግር መባባስ
ለነርሱ ፀረ አብዮት አመጽ ተለቀ አመቺ ሁኔታ እንደሚፈጥር እንደገባቸው ያሳያል::በአንፃሩ፣
የሰፊውን ሕዝብ ወገንነት የመረጡ ተራማጆች ደግሞ ይህ የኢኮኖሚ ችግር ለፀረ አብዮት ቀለበሳ
እንዳይመች ብቻ ሳይሆን የሰፊው ሕዝብ አለታፂ ችግሮች መፍትሄ እያገኙ እንዲሄዱም መታገል
ይኖርባቸዋል::

የሥራ አጡንና የቦዘኔዎችን ችግር በሚመለከተው በኩል፤አገራችን ዛሬም ወደኋላ የቀረች አገር መሆንዋን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ኢንዱስትሪ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ተስፋፍቶ ሥራ አጡንና ቦዘኔውን በኢንዱስትሪ ሥራ ላይ ማሰማራት አይቻልም፡፡ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት እንደልብስ ሰሪዎችና የመሳሰሉት የእደ ጥበብ ሥራዎች በሕብረት እንዲደራጁና ደግሞ መለስተኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲያድጉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡እነዚህን የእደ ጥበብ ሥራዎችና የኢትዮጵያን ሥራ አጥና ቦዘኔ ቁጥር ስናነፃፅር በዚህ በኩል ሊገኝ የሚችለው ጥቅም አነስተኛው ክፍል ብቻ ነው፡፡በሌላ በኩል፤በአዲስ አበባ ዙሪያ ብቻ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሥራ አጦችንና ቦዘኔዎችን በአትክልት፤ፍራፍሬና ችግኞችን በመትከል ሥራ ማሰማራት ይቻላል፡፡ይህ ዓይነቱ የአረንጓዴ መቀነት እቅድ በመባል የሚታወቀው የማሰማራት ዘዴ ባንድ በኩል ባጭር ጊዜ ውስጥ ከሥራ አጡና ከቦዘኔዎች የተወሰነውን ክፍል ሥራ ለማስያዝ ሲጠቅም፤በሌላ በኩል እንደዚህ ዓይነቶችን የእርሻ ምርቶች ከፍ ለማድረግ ያስችላል፡፡ሥራ አጡና ቦዘኔውም ከለመደው የከተማ ኑሮ ብዙ ሳይርቅ ቀስ በቀስ በእርሻ መተዳደርን እንዲለምድ ያደርጋል፡፡በእንደዚህ ዓይነት ብዙ ወጭ የማይጠይቅ ዕቅድ የሥራ አጥ ችግራቸውን ማስታገስ ከቻሉ ሶሺያሊስት አገሮች ኩባን እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡

ሆኖም፤እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ሁሉ ገፋ ቢል ከፊል መፍትሄ ቢሆኑ ነው፡፡የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዋና መሰረት እርሻ ነው፡፡ስለዚህ ሥራ አጡንና ቦዘኔውን በአስቸኳይና ዋስትና ባለው መንገድ ሥራ ለማስያዝ ከተፈለገ ዋናው እነኚህን በእርሻ ሥራ ላይ ማሰማራት ነው፡፡ይህ ሲመከር ባንድ በኩል ከተማ መኖር የለመዱ ሥራ አጦችና ቦዘኔዎች/በተለይም ቦዘኔዎች/ከገጠር ኑሮ ጋር እንደገና ለመላመድ ያስቸግራቸዋል፡፡በሌላ በኩልም፤የተገኘችዋንም ገቢ በቀን በቀኑ ማግኘት የለመዱ ሥራ አጦችና ቦዘኔዎች/በተለይም ቦዘኔዎች/ገቢያቸውን ዓመት ጠብቆ ማግኘትን እንደችግር መመልከታቸው አለ፡፡በዚህም ላይ ከሥራ አጥነት ጋር ተያይዞ የመጡ፤በተለይም በቦዘኔው ላይ ጎልተው የሚታዩ ለዲሲፕሊንና ትዕግስት ለሚጠይቁ ሥራዎች ጠንቅ የሆኑ ጠባዮች አሉ፡፡እነዚህ ሁሉ ችግሮች የሚወገዱት በእርሻ ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ሥራ አጦችና ቦዘኔዎች በቂ ፖለቲካዊ ትምህርት በመስጠት ንቃታቸውን እንዲያዳብሩ በማድረግ ነው፡፡ንቃታቸውን በማሳደግና የመቋቋሚያ እርዳታ በመስጠት ሥራ አጦችንና ቦዘኔዎችን በእርሻ ሥራ ማሰማራት የአገሪቷን ሥራ አጥ ችግር ማስወገጃ ብቻ ሳይሆን ለኢኮኖሚያዊ እድገታችም ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡

የኑሮ ውድነትንና የእቃዎችን ከገበያ መጥፋት በሚመለከተው በኩል፤ትላልቅ የማከፋፈያ ድርጅቶች/በተለይ ከውጭ ለሚመጡ እቃዎች/ ተወርሰው በመንግስት ቁጥጥር ሥር መዋል አለባቸው፡፡በዚህም፤በተጭበረበረ ፋክቱርና በሌላም ዘዴ በነዚህ አስመጪና ላኪዎች ድርጅቶች የሚሰረቀው የአገሪቷ ገንዘብ አገር ውስጥ ቀርቶ በሥራ ላይ ይውላል፡፡በተጨማሪም፤በነዚህ ማከፋፈያ ድርጅቶች የሚሰራው አሻጥር ገደብ ያገኝና ከውጭ የሚመጡ ዕቃዎች የተመረጡ፤ለሰፊው ሕዝብ ጥቅምና አገልግሎት ተፈላጊ የሆኑ ብቻ ይሆናሉ፡፡እነዚህም እንደየአስፈላጊነታቸው ይከፋፈላሉ፤ዋጋቸውም ከሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ከዚህም በላይ፤በሸማቾችና በአምራቾች መሃል ሆነው የሚያሻጥሩ ነጋዴዎችን ለመቋቋም፤መንግስት የራሱን የማከፋፈያ ጣቢያዎች መክፈት አለበት፡፡በተጨማሪም የከተማው ሰርቶ አደር የሕብረት ሥራ ሱቆች እንዲመሰርቱ መረዳት አለባቸው፡፡የገበሬ ማህበራትም በማህበራቸው ስር የሕብረት ንግድ እንዲያቋቁሙ መታገዝ አለባቸው፡፡እነዚህ ሲፈጸሙ፤ነጋዴዎች የግድ ከነዚህ ከሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ከሚሸጡ መንግስታዊና ሕዝባዊ ማከፋፈያዎች ጋር መወዳደር ስለሚገደዱ ዛሬ እንደሚያደርጉት ዋጋቸውን እንደፈለጉት የመስቀል እድል አይኖራቸውም፡፡

ከነዚህ በተረፈ፤የቢሮክራሲውን አሻጥርና አሻጥረኞችን መደገፍ መቋቋም የሚቻለው በቅርብ ጊዜ ሲታይ ቢሮክራሲውን በጥብቅ በመቆጣጠርና በማፅዳት ነው፡፡መሰረታዊ መፍትሄው ግን ለሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በማክበር ነው፡፡ቢሮክራሲው በሥልጣኑ ተጠቅሞ የሚሰራውን አሻጥር ባጠቃላይና ተጠያቂ የሆኑ ግለሰቦችን ለማጋለጥ የሚቻለው ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሲከበሩ ነው፡፡በሥልጣን ሌላ ነገር ሠርቶ በአፍ የሕዝብ ደጋን እየመሰሉ ማደናበር የሚቀረው፤ሁሉም በሰራው የሚፈተንበት ሁኔታ የሚፈጠረውም ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለሰፊው ሕዝብ ሲከበሩ ነው፡፡ሰፊው ሕዝብ የእለት ችግሮቹን ተጨባጭ ምክንያቶች ጠንቅቆ የሚረዳውና ለመፍትሄዎቹ መታገል የሚችለው ሌሎች እናስብልሃለን በሚሉት ሳይሆን ዲሞክራሲያዊ መብቶቹን በጁ ጨብጦ ሲታገል ነው፡፡

እንደገመገምነው፤የዛሬው የኢኮኖሚ ችግር የኢትዮጵያን አብዮት ዕድል ከሚወስኑት ከፍተኛ ጉዳዮች አንደኛው ነው፡፡የሰፊው ሕዝብ እለታዊ ችግሮች እንዲወገዱ፤ለዘለቄ መፍትሄና ለዘለቄ ድሉ በሙሉ ኃይሉ እንዲሰለፍ መታገል አጣዳፊ ሃላፊነት ነው፡፡በዚህም አንፃር፤ሰፊው ሕዝብ፤በእለታዊ ችግሩ እየተጠቀሙ የአዞ እንባ በሚያነቡ ጠላቶቹ ቅስቀሳ ተጥቆ እንዳይፈታ፤በነዚህ እለታዊ ችግሮቹ ላይ ተራምዶ ለዘለቄ መፍትሄዎቹ ግፉ እንዲሰለፍ ንቃቱ ማደግ ድርጅቱ መጠናከር አለበት፡፡አብዮተኛ ተራማጆችም የሰፊውን ሕዝብ እለታዊ ችግሮች ችላ ብለው ለዘላቂ ግቡ ሊያሰልፉት እንደማይችሉ ተረድተው፤እነዚህን እለታዊ ችግሮች ለማስወገድ በሚደረገው ትግል በግንባር ቀደምነት መሰለፍ አለባቸው፡፡

የሰፊውን ሕዝብ እለታዊ ችግሮች ለማስወገድ ተጨባጭ እርምጃዎች ይወሰዱ

የቢሮክራሲው አሻጥርና አሻጥረኞችን ማገዝ ደገታ ዱሉ የሰፊው ሕዝብ ነው